የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ ጥር ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 9
ADDIS ABABA, 12th January 2017


<u>ማውጫ</u>

**CONTENT**


አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፮/፪ሺ፱ ዓ.ም

ከፑሽኪን አደባባይ እስከ ጎተራ ማሳለጫ ላለው መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክ መንግስት የተገኙ ብድሮች ማፅደቂያ አዋጅ .... ገፅ ፱ሺ፭፻፫

Proclamation No.986/2017

People's Republic of China Loan Agreement for financing Pushikin to Gottera Road Project Ratification Proclamation page .......................................... 9503


**አዋጅ ቁ□ር ፱፻፹፮/፪ሺ፱**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ከፑሽኪን አደባባይ እስከ ጎተራ ማሳለጫ ያለውን መንገድ ለመገንባት የተደረጉ የብድር ስምምነቶችን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ከፑሽኪን አደባባይ እስከ ጎተራ ማሳለጫ ላለው መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፫፻፷ ሚሊዮን የቻይና ዩዋን (ሶስት መቶ ስልሳ ሚሊዮን የቻይና ዩዋን) የሆነ የሚያስገኙ የብድር ስምምነቶች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሐምሌ ፲፫ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም፣ ሚያዚያ ፲ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ፣ ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም፣ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ፣ጥቅምት ፲፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም እና ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረሙ በመሆኑ፤

እነዚህን የብድር ስምምነቶች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

**PROCLAMATION No.986 /2017**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT FOR FINANCING PUSHIKIN TO GOTTERA ROAD PROJECT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMNET OF THE PEOPLE'S REPUBLIC OF CHINA**

**WHERE AS**, Loan Agreements between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People's Republic of China stipulating that the People's Republic of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia Loans in an amount equivalent to three hundred sixty million Chinese Yuan (360,000000 Chinese Yuan) for financing Pushikin to Goterra Road Project was signed in Addis Ababa on the 20th day of July 2010, 18th April 2011, 15th August 2011,28th January 2012, 29th October 2012 and 24th day of May 2013,

**WHERE AS,** the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on the 27th day of December, 2016,

ታህሳስ ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የፀደቃቸው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል:-

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “ከፑሽኪን አደባባይ እስከ ጎተራ ማሳለጫ ላለው መንገድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክ መንግስት የተገኙ ብድሮች ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፮/፪ሺ፱” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪.<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በህዝባዊት ቻይና ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሐምሌ ፲፫ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም፣ ሚያዚያ ፲ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ፣ ነሐሴ ፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም፣ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ፣ጥቅምት ፲፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም እና ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረሙት የብድር ስምምነቶች በዚህ አዋጅ ፀድቀዋል፡፡

**፫.<u>የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን</u>**

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቶቹ የተገኘውን ፫፻፷ ሚሊዮን የቻይና ዩዋን (ሶስት መቶ ስልሳ ሚሊዮን የቻይና ዩዋን) በብድር ስምምነቶቹ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “People’s Republic of China Loan Agreement for financing Pushikin to Gottera Road Project Ratification Proclamation No.986/2017”.

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan agreement signed on the 20th day of July 2010, 18th April 2011, 15th August 2011, 28th January 2012, 29th October 2012 and 24th day of May 2013 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the People’s Republic of China are hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilisation of the Loan amount of three hundred sixty million Chinese Yuan (360,000,000 Chinese Yuan ) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4.<u>Effective Date</u>**

Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of January, 2017**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**12. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as

**Done at Addis Ababa, this day of December, 2016**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**Done at Addis Ababa, this 1st day of November, 2016**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**